**ለተቀባዮች እና ለእንክብካቤ አቅራቢዎች የመረጃ ወረቀት**

# ዕድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች የኮሮናቫይረስ በሽታ 2019 (covid-19) ን ለመከላከል የPFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት የድንገተኛ አጠቃቀም ፈቃድ (EUA)

በ SARS-CoV-2 የተከሰተዉን የኮሮና ቫይረስ በሽታ 2019 (COVID-19) ለመከላከል የ Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት ቀርቦሎታል ። ይህ የመረጃ ወረቀት በአሁኑ ወቅት የ COVID-19 ወረርሽኝ በመኖሩ ምክንያት የሚወስዱትን የ Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት ጉዳቶች እና ጥቅሞችን መረዳት እንዲችሉ የሚረዳን መረጃ የያዘ ነው።

Pfizer-BioNTech ክትባት  በCOVID-19 በ COVID-19 እንዳይያዙ ይከላከላል ። COVID-19 ን ለመከላከል በአሜሪካ የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር (FDA) የጸደቀ ክትባት የለም።

ስለ Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት መረጃ ለማግኘት ይህንን የመረጃ ወረቀት ያንብቡ። ጥያቄዎች ካሉዎት የክትባት አቅራቢውን ያነጋግሩ ። Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባትን መቀበል የእርስዎ ምርጫ ነው።

Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት እንደ 2-ልኬት/ዶዝ በተከታታይ በ 3 ሳምንታት ልዩነት በ ጡንቻ ላይ ይሰጣል ።

Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት ሁሉንም ሰው ከበሽታው ላይጠብቅ ይችላል ።

ይህ የመረጃ ወረቀት ተሻሽሎ ሊሆን ይችላል። በጣም በቅርብ ጊዜ የወጣውን   የመረጃ ወረቀት ለማግኘት እባክዎ www.cvdvaccine.com ን ይመልከቱ።

## **ይህንን ክትባት** ከመውሰድዎ **በፊት ማወቅ ያለብዎት ነገር**

## COVID -19 ምንድን ነው?

COVID-19 በሽታ SARS-CoV-2 ተብሎ በሚጠራው ኮሮናቫይረስ ይከሰታል ። የዚህ አይነቱ ኮሮናቫይረስ ከዚህ በፊት አልታየም ። ቫይረሱ ካለበት ከሌላ ሰው ጋር በመገናኘት በ COVID-19 ሊያዙ ይችላሉ ። እሱም ሌሎች አካላትን ሊጎዳ የሚችልበአብዛኛው  የመተንፈሻ አካላት በሽታ ነው ። በ COVID-19 የተያዙ ሰዎች ከቀላል ምልክቶች እስከ ከባድ ህመም ድረስ የተለያዩ ምልክቶች እንደሚታዩባቸው ሪፖርት ተደርጓል ። በቫይረሱ ከተያዙ ከ 2 እስከ 14 ቀናት በኋላ ምልክቶቹ ሊታዩ ይችላሉ ። ምልክቶቹ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡ ትኩሳት ወይም ብርድ ብርድ ማለት፣ ሳል፣ የትንፋሽ እጥረት፣ ድካም፣ የጡንቻ ወይም የአካል ህመም፣ ራስ ምታት፣ አዲስ የጣእም ወይም የሽታ ስሜት ማጣት፣ የጉሮሮ መቁሰል፣ የአፍንጫ መደፈን ወይም ፈሳሽ፣ ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ፣ ተቅማጥ።

## PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት ምንድነው?

Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት ከ COVID-19 ሊከላከል የሚችል ያልተረጋገጠ ክትባት ነው።

Revised: 25 June 2021

COVID-19 ን ለመከላከል በ FDA የተረጋገጠ ክትባት የለም ።

በድንገተኛ ጊዜ አጠቃቀም ፈቃድ (EUA) መሰረት ዕድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦችን ከ COVID-19 ለመከላከል FDA ለ Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት ድንገተኛ አጠቃቀም ፈቅዷል ።

EUA ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት **"የድንገተኛ ጊዜ አጠቃቀም ፈቃድ ("What is an Emergency Use Authorization (EUA)?" ምንድነው?"** የሚለውን ክፍል በዚህ የመረጃ ወረቀት መጨረሻ ላይ ያግኙ።

## PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት ከማግኘትዎ በፊት ለክትባትዎ አቅራቢ ምን መንገር አለብዎት?

**የሚከተሉትን ጨምሮ ለክትባት አቅራቢው ስለ ሁሉም የጤንነትዎ ሁኔታ ይናገሩ:**

- ማንኛውም አይነት አለርጂዎች ካለብዎት
- ማዮካርዳይቲስ ካለበት (የልብ ጡንቻ ማመርቀዝ) ወይም ፔሪካርዳይቲስ (የልብ ውጫዊ ከባቢ ማመርቀዝ)
- ትኩሳት ካለበት
- የደም መፍሰስ ችግር ካለብዎ ወይም በደም ማቅጠኛ መሳሪያ የሚጠቀሙ ከሆነ
- በሽታ የመከላከል አቅም ከሌልዎት ወይም በሽታ የመከላከል ስርዓትዎን የሚነካ መድሃኒት የሚወስዱ ከሆነ
- ነፍሰ ጡር ከሆኑ ወይም ለማርገዝ አቅደው ከሆነ
- ጡት እያጠቡ ከሆነ
- ሌላ የ COVID-19 ክትባት ወስደው ከሆነ
- መርፌ መዋጋት ጋር በተያያዘ ራስዎን ስተው የሚያውቁ ከሆነ

## የ PFIZER-BIONTECH COVID-19 ን ክትባት ማን ማግኘት አለበት?

ዕድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባትን ለድንገተኛ ጊዜ አጠቃቀም FDA ፈቅዷል ።

## PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባትን ማግኘት <u>የሌለበት</u> ማን ነው?

የሚከተሉት የታዩብዎት ከሆነ የ Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት መውሰድ የለብዎትም፡

- ከዚህ በፊት የዚህን ክትባት ዶዝ ሲወስዱ ከባድ የሆነ የአላርጂ ችግር ካጋጠመዎት
- ለዚህ ክትባት ማንኛውም ንጥረ ነገር ከባድ የአለርጂ ችግር ካለብዎት

## በ PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት ውስጥ ያሉት ንጥረ ነገሮች ምንድናቸው?

Pfizer BioNTech COVID-19 ክትባት የሚከተሉትን ንጥረ ነገሮች በውስጡ ይዟል፡ mRNA ፣ ሊፒድስ ((4-hydroxybutyl) azanediyl)bis(hexane-6,1-diyl)bis(2-hexyldecanoate)፣ 2 [(polyethylene glycol) -2000] - N ፣ N-ditetradecylacetamide ፣ 1,2-Distearoyl-sn-glycero-3- phosphocholine ፣ እና ኮሌስትሮል) ፣ ፖታሲየም ክሎራይድ ፣ ሞኖቤዚክ ፖታስየም ፎስፌት ፣ ሶድየም ክሎራይድ ፣ ዳይቤዚክ ሶዲየም ፎስፌት ዳይሃይድሬት እና ሱክሮስ።

## የ PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት እንዴት ይሰጣል?

Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት በጡንቻ ላይ እንደ መርፌ ይሰጥዎታል።

Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት እንደ 2-ልኬት/ዶዝ በተከታታይ በ 3 ሳምንታት ልዩነት ይሰጣል ፡፡

የ Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት አንድ ዶዝ/ልኬት ከተቀበሉ በኋላ የክትባቱን ተከታይ ለማጠናቀቅ ከ 3 ሳምንት በኋላ የዚህኑ ተመሳሳይ ክትባት ሁለተኛ ዶዝ መቀበል አለብዎት ፡፡

**PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት ከዚህ በፊት ጥቅም ላይ ውሎ ያውቃል?**

Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት ያልተረጋገጠ ክትባት ነው ፡፡ በክሊኒካዊ ሙከራዎች ለይም ዕድሜያቸው ከ 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ በግምት ወደ 23ሺህ የሚጠጉ ግለሰቦች ቢያንስ 1 ዶዝ/ልኬት የሚሆን የ Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት አግኝተዋል ፡፡

**የ PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት ጥቅሞች ምንድ ናቸው?**

በመካሄድ ላይ ባለው ክሊኒካዊ ሙከራ ውስጥ ፣ Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት በ 3 ሳምንታት ልዩነት በተሰጡ 2 ልኬቶች ተከትሎ COVID-19 ን ለመከላከል ተችሏል ፡፡ ከ COVID-19 ለምን ያህል ጊዜ እንደሚከላከል እስካሁን አልታወቀም።

**የ PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት ስጋቶች ምንድን ናቸው?**

የ Pfizer-BioNTech የ COVID-19 ክትባት ከባድ የአለርጂ ግብረ መልስ ሊያከትል የሚችልበት የሩቅ እድል አለ። ከባድ የአለርጂ ግብረ መልስ ብዙውን ጊዜ የ Pfizer-BioNTech የ COVID-19 ክትባት ዶዝን ከወሰዱ በኋላ ከጥቂት ደቂቃዎች እስከ አንድ ሰአት ውስጥ ሊከሰት ይችላል። በዚህም ምክንያት፣ የክትባት አቅራቢዎ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ እንዲከታተልዎ ክትባቱን የወሰዱበት ቦታ ላይ እንዲቆዩ ሊጠይቅዎት ይችላል። የከባድ የአለርጂ ግብረ መልስ ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

- የመተንፈስ ችግር
- የፊትዎ እና ጉሮሮዎ እብጠት
- ፈጣን የልብ ምት
- በመላ ሰውነትዎ ላይ መጥፎ ሽፍታ
- መፍዘዝ እና ድካም

የ Pfizer-BioNTech የ COVID-19 ክትባትን የወሰዱ የተወሰኑ ሰዎች ላይ ማዮካርዳይቲስ (የልብ ጡንቻ ማመርቀዝ) እና ፔሪካርዳይቲስ (የልብ ውጫዊ ከባቢ ማመርቀዝ) ተከስቷል። ከእነዚህ አብዛኞቹ ሰዎች ውስጥ፣ የ Pfizer-BioNTech የ COVID-19 ክትባትን ሁለተኛ ዶዝ ከተቀበሉ በኋላ በጥቂት ቀናት ውስጥ ምልክቶች ጀምረዋል። ይህ የመከሰት እድሉ በጣም ዝቅተኛ ነው። የ Pfizer-BioNTech የ COVID-19 ክትባትን ከተቀበሉ በኋላ የሚከተሉት ምልክቶች ካለብዎት ወዲያውኑ የህክምና ትኩረት መሻት አለብዎት፡-

- የደረት ህመም
- የትንፋሽ ማጠር
- የፈጣን ትንፋሽ፣ መርገብገብ፣ መንቀጥቀጥ፣ ወይም የልብ መምታት ስሜቶች

ከ Pfizer-BioNTech የ COVID-19 ክትባት ጋር ሪፖርት የተደረጉ የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ከባድ የአለርጂ ግብር መልሶች
- ሽፍታ፣ ማሳከክ፣ የሚያሳክኩ ሽፍታዎች፣ ወይም የፊት ማበጥ የመሳሰሉ ከባድ ያልሆኑ የአለርጂ ግብረ መልሶች
- ማዮካርዳይቲስ (የልብ ጡንቻ ማመርቀዝ)

- ፔሪካርዳይቲስ (የልብ ውጫዊ ከባቢ ማመርቀዝ)
- መርፌ የተወጋበት ቦታ ህመም
- ሲንካ የሚሰማ ህመም
- ራስ ምታት
- የጡንቻ ህመም
- ብርድ ብርድ ማለት
- የመገጣጠሚያ ህመም
- ትኩሳት
- መርፌ የተወጋበት ቦታ እብጠት
- መርፌ የተወጋበት ቦታ መቅላት
- ማቅለሽለሽ
- የጤነኝነት ስሜት አለመስማት
- ያበጡ ሊምፍ ኖዶች (ሊምፋዴኖፓቲ)
- ተቅማጥ
- ትውከት
- የእጅ ህመም

እነዚህ ሁሉም የ Pfizer-BioNTech የ COVID-19 ክትባት የጎንዮሽ ጉዳቶች ሊሆኑ አይችሉም። ከባድ እና ያልተጠበቁ የጎንዮሽ ጉዳቶች ሊከሰቱ ይችላሉ። የ Pfizer-BioNTech የ COVID-19 ክትባት አሁንም በክሊኒካል ሙከራዎች እየተጠና ነው።

**ስለ የጎንዮሽ ጉዳቶቹ ምን ማድረግ አለብኝ?**

ከባድ የአለርጂ ችግር ካጋጠምዎት ለ 9-1-1 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው ሆስፒታል ይሂዱ ።

የሚያስቸግርዎ ወይም የማይጠፋ የጎንዮሽ ጉዳት ካለዎት ለክትባት አቅራቢው ወይም ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ይደውሉ ።

የክትባት የጎንዮሽ ጉዳቶችን **ለ FDA/CDC ክትባት አሉታዊ ክስተት ሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት ስርዓት(Vaccine Adverse Event Reporting System VAERS)** ሪፖርት ያድርጉ ። የ VAERS ከክፍያ ነፃ ቁጥር 1-800-822-7967 ላይ ይደውሉ ወይም በመስመር ላይ ወደ https://vaers.hhs.gov/reportevent.html ሪፖርት ያድርጉ። እባክዎ “Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት EUA” የሚለውን በሪፖርቱ ቅፅ #18 ሳጥን የመጀመሪያ መስመር ውስጥያካትቱ ።

በተጨማሪም ከዚህ በታች በተጠቀሰው የግንኙነት መረጃ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ለ Pfizer Inc. ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ ።

| ድረ-ገፅ | የፋክስ ቁጥር | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|
| www.pfizersafetyreporting.com | 1-866-635-8337 | 1-800-438-1985 |

v-safe ውስጥ ለመመዝገብ አማራጭ ሊሰጥዎት ይችላል። V-safe አዲስ በበጎ ፍቃድ የሚደረግ ስማርት ስልክን መሰረት ያደረገ መሳሪያ ሲሆን የ COVID-19 ክትባት ከወሰዱ በኋላ ሊከሰቱ የሚችሉ የጎንዮሽ

ጉዳቶችን ለመለየት ክትባት የወሰዱ ሰዎችን ለመከታተል የጽሁፍ መልእክት እና የድር የዳሰሳ ጥናቶችን ይጠቀማል። V-safe CDC የ COVID-19 ክትባቶችን ደህንነት እንዲቆጣጠር የሚረዱ ጥያቄዎችን ይጠይቃል። V-safe አስፈላጊ ከሆነ የሁለተኛ-ዶዝ ማስታወሻዎሽን እንዲሁም ተሳታፊዎች የ COVID-19 ክትባትን ተከትሎ ከፍተኛ የጤና ተጽእኖን ሪፖርት ካደረጉ በ CDC የቀጥታ የስልክ ክትትልን ያቀርባል። እንዴት መመዝገብ እንዳለብዎት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የሚከተለውን ይጎብኙ፡- www.cdc.gov/vsafe።

## PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት ላለመዉሰድ ከወሰንኩስ?

Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባትን መቀበል ወይም አለመቀበል የእርስዎ ምርጫ ነው። ላለመቀበል ከወሰኑ መደበኛ የሕክምና እንክብካቤዎን አይለውጠውም ።

## ከ PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት በተጨማሪ COVID-19 ን ለመከላከል ሌሎች ምርጫዎች አሉ?

በአሁኑ ሰአት፣ COVID-19 ን ለመከላከል ፍቃድ ያገኘ አማራጭ ክትባት የለም። COVID-19 ን የሚከላከሉ ሌሎች ክትባቶች በድንገተኛ አጠቃቀም ፍቃድ መሰረት ሊኖር ይችላሉ።

## ከሌሎች ክትባቶች ጋር የ PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት መቀበል እችላለሁ?

የ Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባትን ከሌሎች ክትባቶች ጋር መጠቀምን አስመልክቶ እስካሁን ምንም መረጃ የለም።

## እርጉዝ ወይም ጡት የማጠባ ብሆንስ?

እርጉዝ ከሆኑ ወይም የሚያጠቡ ከሆነ አማራጮችዎን ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይወያዩ ።

## PFIZER-BIONTECH COVID-19 ክትባት በ COVID-19 በሽታ እንድያዝ ያደርገኛል?

የለም። Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት SARS-CoV-2 ን አያካትትም እናም በ COVID-19 ሊያስይዝዎ አይችልም።

## የክትባት ካርድዎን ያስቀምጡ

የመጀመሪያውን ክትባት/ዶዝ ሲወስዱ ለሁለተኛው የ Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት/ዶዝ መቼ ተመልሰው መምጣት እንዳለብዎ ለማሳየት የክትባት ካርድ ያገኛሉ። ሲመለሱ ካርድዎን ይዘው መምጣትዎን ያስታውሱ ።

## ተጨማሪ መረጃ

ጥያቄዎች ካሉዎት ድረ-ገፁን ይጎብኙ ወይም ከዚህ በታች በተጠቀሰው የስልክ ቁጥር ይደውሉ።

በጣም የቅርብ ጊዜዎቹን የእውነታ ወረቀቶች ለማግኘት እባክዎን ከዚህ በታች የቀረበውን የ QR ኮድ ይቃኙ።

| አለም አቀፍ ድረ-ገፅ | ስልክ ቁጥር |
| --- | --- |
| www.cvdvaccine.com | 1-877-829-2619<br>(1-877-VAX-CO19) |

**የበለጠ ማወቅ የምችለው እንዴት ነው?**

- የክትባት አቅራቢውን ይጠይቁ ፡፡
- CDC በ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/index.html. ላይ ይጎብኙ
- FDA በ https://www.fda.gov/emergency-preparedness-and-response/mcm-legal-regulatory-and-policy-framework/emergency-use-authorization ላይ ይጎብኙ
- የአካባቢዎን ወይም የክልልዎን የህዝብ ጤና ክፍልን ያነጋግሩ።

**የ የክትባት መረጃዬ የት ተመዝግቦ ይቀመጣል?**

የክትባት አቅራቢው የክልል / የአካባቢዎ የክትባት መረጃ ስርዓት (IIS) ወይም ሌላ በተሰየመ ስርዓት ውስጥ የክትባት መረጃዎን ሊያካትት ይችላል ፡፡ ይህ ለሁለተኛው ክትባት ሲመለሱ ተመሳሳይ የሆነ ክትባት እንዳገኙ ያረጋግጥልዎታል ፡፡ ስለ IISs ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይህንን ይጎብኙ፡ https://www.cdc.gov/vaccines/programs/iis/about.html

**ለ COVID-19 ክትባት ደረሰኝ አስተዳደራዊ ክፍያ ልከፍል እችላለው?**

አይ። በዚህ ሰአት፣ አቅራቢው ለክትባት ዶዝ ሊያስከፍልዎ አይችልም እናም የ COVID-19 ክትባትን ብቻ እየተቀበሉ ከሆነ የክትባት አስተዳደር ክፍያ ወይም ሌላ ክፍያ ከኪስዎ ወጪ አድርገው ሊከፍሉ አይችሉም። ሆኖም፣ ክትባት አቅራቢዎች ለክትባት ተቀባዩ የ COVID-19 አስተዳደር ክፍያዎችን ከሚሸፍን ፕሮግራም ወይም እቅድ ተገቢ ማወራረጃ ሊፈልግ ይችላል (የግል መድህን፣ Medicare፣ Medicaid፣ የጤና ሀብቶች እና አገልግሎቶች አስተዳደር [HRSA] የ COVID-19 መድህን ለሌላቸው ተቀባዮች መድህን የሌለው ፕሮግራም)።

**የተጠረጠረ ማጭበርበርን የት ሪፖርት ማድረግ እችላለው?**

የ CDC COVID-19 ክትባት ፕሮግራም መስፈርቶች ማንኛውም ጥሰቶችን የሚያውቁ ግለሰቦች ወደ ኢንስፔክተር ጄነራል መስሪያ ቤት፣ U.S. ሪፖርት እንዲያደርጉ ይበረታታሉ። የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፣ በ 1-800-HHS-TIPS ወይም https://TIPS.HHS.GOV።

**የመከላከያ እርምጃዎች(COUNTERMEASURES) የጉዳት ካሳ ፕሮግራም ምንድነው?**

የመከላከያ እርምጃዎች(COUNTERMEASURES) የጉዳት ካሳ ፕሮግራም (CICP) የፌዴራል ፕሮግራም ሲሆን ይህንን ክትባት ጨምሮ በተወሰኑ መድኃኒቶች ወይም ክትባቶች ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው የተወሰኑ ሰዎች ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉ ወጪዎችን እና ለሌሎች ልዩ ወጪዎች በመክፈል ድጋፍ ሊያደርግ የሚችል ተቋም ነው። ባጠቃላይ ክሱ ክትባቱን ከተቀበሉበት ቀን አንስቶ በአንድ (1) ዓመት ውስጥ ለ CICP መቅረብ አለበት ፡፡ ስለዚህ ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ www.hrsa.gov/cicp/ ን ይጎብኙ ወይም በ 1-855-266-2427 ላይ ይደውሉ ፡፡

**የአስቸኳይ ጊዜ አጠቃቀም ፍቃድ (EUA) ምንድን ነው?**

የአሜሪካ ሀገር FDA የ Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት EUA ተብሎ በሚጠራው የድንገተኛ ጊዜ ተደራሽነት ዘዴ ስር እንዲገኝ አድርጎታል ። EUA በ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት የመድኃኒት እና የባዮሎጂያዊ ምርቶች ድንገተኛ አጠቃቀምን ለማስረዳት ሁኔታዎች እንዳሉ በጤና እና በሰብአዊ አገልግሎቶች ሴክሪተሪ (HHS) መግለጫ የተደገፈ ነው ።

Pfizer-BioNTech COVID-19 ክትባት በ FDA ከተረጋገጠዉ ወይም ከተጣራ ምርት ጋር አንድ ዓይነት ግምገማ አልተደረገለትም ። FDA የተወሰኑ መመዘኛዎች ሲሟሉ EUA ን ስራ ላይ ሊያውል ይችላል ይህም በቂ ፣ የተፈቀዱ ፣ ተደራሽ የሆኑ አማራጮች በሌሉበት ጊዜ ነው ። በተጨማሪም የ FDA ውሳኔ በ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት ምርቱ COVID-19 ን ለመከላከል ውጤታማ ሊሆን በሚችልበት አጠቃላይ የሳይንሳዊ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ ሲሆን የምርቱ የታወቁ እና ያላቸው እምቅ ጥቅሞች ከሚታወቁ እና ሊኖሩዋቸው ከሚችሉት ጉዳቶች ሊበልጥ ይገባል። ምርቱን በ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት ለታካሚዎች ሕክምና እንዲውል ለማስቻል እነዚህ ሁሉ መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው ።

ለ Pfizer-BioNTech ክትባት EUA ካልተቋረጠ ወይም ካልተሻረ በስተቀር (ምርቶቹ ከዚያን በኋላ አገልግሎት ላይ መዋል የማይችሉ ከሆነ) የእነዚህ ምርቶች የድንገተኛ ጊዜ አጠቃቀምን በማረጋገጥ ለ COVID-19 አዋጅ እስከምቆይበት ግዜ ተግባራዊይሆናል

Pfizer

የተመረተው በ
Pfizer Inc., New York, NY 10017

BIONTECH

የተመረተው ለ
BioNTech Manufacturing GmbH
An der Goldgrube 12
55131 Mainz, Germany
LAB-1451-4.2a
ክለሳ የተደረገው፡- 25 ጁን 2021

Scan to capture that this Fact Sheet was provided to vaccine recipient for the electronic medical records/immunization information systems.

ባርኮድ ቀን፡- 05/2021